# ክላሚድያ፡ የህመምተኛ መረጃ (2016-10-21)

የተላልፊ በሽታ መከላከያ ሃኪሞች፤ የተላላፊ በሽታ መከላከያ ልሳን።

## ይህ መረጃ እንዲደርሶት ለምን አስፈለገ?

በክላሚድያ በተባለው በሽታው ተለክፋዋል ወይም ተለክፈው እንዳይሆን ተጠርጥራዋል። ይህ የመረጃ ጽሁፍ፡
ክላሚድያ ከተባለው በሽታ፡ እንዴት እንደሚድኑ እና ምን ማድረግ እንደሚገባዎት ማብራሪያ ይሰጣል።

## ክላሚድያ ምንድን ነው?

ክላሚድያ አንድ የባክተሪያ ዓይነት ነው፤ ኣብዛኛውም ጊዜ በወንዱ የሽንት አገዳና፡ በሴቶቹ እምስ፡ እንዲሁም
በትልቁ አንጀት የሚሰፍር ነው። አንዳንድ ጊዜ በጉሮሮ ውስጥም ሊገኝ ይችላል። ሰው የክላሚድያ ባክተሪያ
እንዳለው ሳያውቅ ረጅም ጊዜ ሊሆነው፤ አንዳንዴም ልብ ሳይል ለብዙ ዓመታት ተለክፎ እንዳለ ሊቆይ ይችላል።

## ክላሚድያ እንዴት ሊይዝ ይችላል?

ክላሚድያ የሚተላልፈው፡ በዋነኛነት፡ ባልተጠበቀ የግብረ–ስጋ ግንኙነት፤ ማለት በእምስ ወይም በቂጥ፡
አንዳንዴም በአፍ በሚደረገው ወሲባዊ ግንኙነት ነው። ብልት በመነካካትና በወሲባዊ አሻንጉሊቶች አመካኝነትም
ባክተሪያው ሊተላለፍ ይችላል። ክላሚድያ በልብስ፡ በፎጣና በሽንት ቤት አመካኝነት **አይተላልፍም**፤ ምክንያቱም
የክላሚድያ ባክተሪያው፡ ከሰው አካል ውጭ መኖር ስለ ማይችል ነው። ሰው በተደጋጋሚ በክላሚድያ መለከፍ
ይችላል።

## ሰው ክላሚድያ እንዳለው እንዴታት ያውቃል?

በክላሚድያ የተለከፉ በርካታ ሰዎች፡ የበሽታ ምልክት የላቸውም፤ በመሆኑም ብዙዎቹ በሽታው እንዳላቸው
አያውቁም። አንዳንዶቹ በሚሸኑበት ጊዜ ሊያማቸው ይችላል።

ሴቶች፡ ደም የተቀላቀለበት ፈሳሽ ሊወጣባቸው ወይም/እንዲሁም በሆዳቸው ዝቅተኛው ክፍል ውስጥ ሊያማቸው
ይችላል። ወንዶች ከሽንቱ አገዳ ፈሳሽ ሊወጣባቸውና በቆለጡ ውስጥ ሊያማቸው ይችላል። ሰው በቂጡ ወሲባዊ
ግንኙነት ካደረገም፤ ከትልቁ አንጀትም ፈሳሽ ሊወጣበት ይችላል። ምንም እንኳ የበሽታው ምልክቶች
ባይታይዎት፤ ክላሚድያ በከፍተኛ ደረጃ ተላላፊ በሽታ ነው።

## ክላሚድያ ምን ያህል አደገኛ በሽታ ነው?

ሴቶች የክላሚድያ ህክምና ባይደረግላቸው፤ በእንቁላል መተላለፍያ አካል ጉዳት ስለሚያደርስ፤ የማፍራት ችግር
ሊያጋጥማቸውና መካን ሊያደርጋቸው ወይም ፅንሰሽሉ ከማኅፀኑ ውጭ እንዲያድግ ሊያደርግ ይችላል።
ወንዶችም በቆለጥቋሮች ውስጥ ልክፈት ሊያጋጥማቸው ይችላል። ክላሚድያ የአይን በሽታና ባጥንት መጋጠሚያዎች
ማሳመም ሊያስከትል ይችላል።

## ክላሚድያ እንዴት መፈወስ ይቻላል?

ክላሚድያ በጸረባክተሪያ መድሃኒት ሊወገድ (ኪኒን) ይቻላል። ኣስፈላጊው መድሃኒት መውሰድና የተሰጥዎት

መምሪያ መከታትል ከጀመሩ፡ በሽታው ይወገዳል። ህክምናው በነጻ ይደረግልዎታል። ሃኪምዎ ከበሽታው ነጻ
መሆንዎ ለመቆጣጠር፡ እንድትመለሱ ቀጥሮት እንደሆነ፡ በቀነ ቀጠሮ መገኘት ይኖርቦታል።
ክላሚድያ እንዳለቦት ከተረጋገጠ፡ **ሌላ ሰው እንዳይበክሉ መጠንቀቅ ይኖርቦታል**። የሚያስተማመንና አደጋን
የማያስከትል፡ ህክምናው እስኪሚጨርሱ ጊዜ፡ ማለት እስከ 10 ቀኖች ድረስ፡ የግብረስጋ ግንኙነት ወይም ሌላ
የወሲብ ተግባር አለማድረግ ነው። የወሲብ ተግባር ካደረጉም፡ ለግብረ አበርዎ ክላሚድያ እንዳሎት መንገር
**አልቦት**። እንዲሁም መከላከያም (ኮንዶም ወይም ፌሚዶን) መጠቀም **አለቦት**።

**የብከላው መስፋፋት ክትትል – ምን ማለት ነው?**
በክላሚድያ የተበከሉ ሰዎች ተከታትለህ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ማድረግ የሚፈለግበት ምክንያትም፡
አንዱ፡ የተለከፉ ሰዎቹን ለማዳንና ከጉዳት ለመከላከል (ላይ ይመልከቱ)፡ ሁለተኛውም፡ የክላሚድያ ብከላው ወደ
ሌሎች እንዳያስተላልፉ ለመግታት ነው።
ካልሚድያ ካልዎት፡ የብከላው መስፋፋት ክትትል ከሚያደርገው ሰው፡ ከማን ወይም ከነማን ጋር፡ እስከ አንድ
ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰው፡ የወሲብ ተግባር እንደፈጸሙ መንገር፤ የመተባበር ግዴታ አለቦት።
ከተከታታዩ ሰው የተናገሩት ሁሉ፡ በምስጢር ይጠበቃል። ሰዎቹ ስለ እነሱ ማን እንዳወራ አያውቁም። እነሱ ማወቅ
ያለባቸው መመርመር እንዳለባቸው ብቻ ነው።

**ክላሚድያ በተላላፊ በሽታዎች ህግ የተመዘገበ ነው – ይህ ምን ማለት ነው?**
በተላላፊ በሽታዎች ህግ ውስጥ፤ እንደ ክላሚድያ የመሳሰሉ በሽታዎች ወደ ሌሎች እንዳይስፋፉ ለመግታት
የተዘገቡ ደንቦችና መምሪያዎች አሉ። በክላሚድያ በሽታው ከተለከፉ ወይም ተለክፈው እንዳይሆን ከተጠረጠሩ፤
ከዶክቶሩ የሚሰጥዎት የሚከተሉትን **መምሪያዎች** መከተል፡ **ግድ ይሆንቦታል**።

- ዶክቶሩ እንድትመለሱ ቀጥሮት እንደሆነ፡ በቀነ ቀጠሮ መገኘት ይኖርቦታል።
- የወሲብ ተግባር ማደረግ ከፈለጉ፡ ለግብረ አበርዎ ክላሚድያ እናዳሎት መንገር አልቦት።
- ህክምናው ከማለቁ በፊት ወይ ምርመራው ሳይጠናቀቅ፡ የወሲብ ተግባር ማድረግ ከፈለጉ፤ መከላከያ
  መጠቀም አለቦት።

በሽታው ለመግታት ስለ ተሰጥዎ ደንብና መምሪያ፡ ስህተት አለው የሚል አስታያየት ካልዎት፤ በሚኖሩበት
አውራጃ የተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ዶክቶር ጋር በመገናኘት ጉዳይዎ እንዲታይ መጠየቅ ይቻላል።

**ተጨማሪ ማወቅ ይፈልጋሉ?**
ስለ ክላሚድያ ተጨማሪ ማብራሪያ በሚከተሉ ድረ-ገጾች ይገኛል።

www.1177.se
www.folkhalsomyndigheten.se
www.umo.se (በድረ-ገጽ የወጣቶች ህክምና መቀበያ)